## “የቅዱሳንን ዐጽመ-ርስት፤ ርኩሣን አይወስዱትም!”
## (የማስጠንቀቂያ ጦማር! ቁ. አንድ)
## ገሞራው - ዘስዊድን

### ለማላከብርዎ ቀማተኛ…

በዚህ ቀዳማዊ ደብዳቤዬ ላይ ብዙኃን ቁምነገሮችን ለማሥፈር፣ እምብዛም አያመቸኝም። ሊመቸኝ ካልቻለበት ወይም ከማይችልበት ምክንያቶች ውስጥ ዓይነተኛውና ተቀዳሚው ስለርስዎ ስለቀማኛው ማንነት በዝርዝር ለማወቅ ባለመቻሌ ነው። ስለ ቤተሰብዎ መሠረት፣ ስለ ሶሻል ዕርከናዊ ደረጃዎ፣ ስለ ትምህርት ጣራዎ፣ ስለሥራ ክፍልዎ፣ ስለ ኑሮ ባሕርይዎ … በዝርዝር ባውቅ ኖሮ፣ በሰፊው አሟልቼ እጅግ በሚያመረቃ አቀራረብ፣ በጻፍኩልዎ ነበር። የእርስዎን ገበናዊ ርዕይ በመላምት ጅምላዊ ትኩረት ሳይ ግን አንድ ነጥብ ፍንትው ብሎ በግልፅና በጉልህ ታይቶኛል። የሰውን መብታዊ ድንበር በመጣስ፣ የሕግን ሉዓላዊ ሕንፃ በመናድ፣ የነፃነትን የሰዎች ፀጋ በማርከስ፣… ከግልዎ ሀብትና ንብረት ውጭ በጊዜያዊ ትምክሕትና በማንአለብኝ ዕብሪታዊ ውጥረት የሌላ ሰው ዐፅመ-ርስት መዝረፍዎ ነው። ይህ ድርጊትዎ ጥሩ ማጋለጫ ስለሚሆን «ቢንጎ!» ብያለሁ።

በተባራሪ ዜና እንደሰማሁት ከሆነ የታላቅና ክቡር ውድ አባት ዐጽመ-ርስት የሆነውንና በይዞታው ንብረትነት ለዘመናት የቆየውን ቦታ ኢሕጋዊ በሆነ መንገድ በዘረፋ ወስደዋል። ይህ ቦታ ለልጆቻቸው በውርስ የተላለፈ ነው። ይህን ቦታ ባለቤቶቹን ሳያማክሩ፣ በጊዜያችን ዘረኞች በፎርፌ ተሰጥቶዎታል። አልፈው ተርፈው ያንን የደረቅ ድንጋይ ካብ እየከመሩበት መሆንዎን በግሌ ካለሁበት ሩቅ ሆኜ ስሰማ በርግጥ ሰማይ የነካ ድፍረትዎን ባይጥመኝም እንኳ አደነቅሁ። ይህን ክቡር ቦታ በስጦታም ይሁን በግዥ መልክ የራሴ አድርጌዋለሁ ብለው እንደሚፎክሩም ሰምቻለሁ። በሁለቱም መልክ ቢሆን የባለቤትነት ምኞትዎ፤ ውሃ ቋጥሮ ሊሳካልዎት የሚችል አይመስለኝም።

ያ ክቡር ቦታ እርስዎ የጥንታዊ ምንነት ታሪኩንና ሉዓላዊ ዝናውን አያውቁ ይሆናል እንጅ በቅድስናቸው አንፃር «ጻድቁ ዮሐንስ» (Prester John) እስከ መባል የበቁ፣ የታላቅ አባት አፅመ-ርስት ነው። በዚህም ክቡር መካን ላይ ለሰማይ የከበዱ አራት ጎምቱ ጎምቱ ልጆች ተወልደው፣ ዕትብታቸው የተቀበረበት ቦታ ነው። በተለይም ያ ቦታ፣ የሃይማኖት ትልቅ አባት የነበሩ ካህን ከ40 ድፍን ዓመታት በላይ ሲፀልዩበት የኖረና በተለይም ከመለስተኛ የቤተ-ክርስቲያን መቅደሳዊ ሕንፃ የማይተናነስ ከፍተኛ ሠቀላ ቤት ሠርተው፣ ብዙኃን ባይተዋር ሕፃናትን ከየቦታው እየሰበሰቡ ሲያስተምሩበት የኖረ ክቡርና ቅዱስ ቦታ ነው። በዚያ ቦታና ቤት ውስጥ ያልተስተናገደ የትውልዱ አንጋፋ ማኅበረሰብ እንደማይገኝ ትልቁም ትንሹም የሚመሠክረው ነው። በተለይም ወገን ረዳት ያጡ ሰዎችን በጥገኝነት አሰባስበው ያሳደጉበትና ያስተማሩበት መካን በመሆኑ ቦታነቱ ክቡርና ቅዱስ ነው። ይህም ቦታ ላለፈው ትውልድ የማደጊያና የመማሪያ ክቡር ቦታ ሆኖ ያገለገለ በመሆኑ፣ ቀሪው ትውልድ በክብር ጠብቆ ያሚያቆየው ታላቅ አፅመ-ርስት ነው። ላለፈው ምዕት ዓመት፣ በሰብዓዊነት አገልግሎት ላይ የቆየ፣ ክቡር መካን በመሆኑም፣ አንድ ታላቅ የመታሰቢያ ሐውልት ታንፆበት (ት/ቤት፣ መጻሕፍት ቤት፣ የሆነ የታሪክ ተቋም (Historical Institute) ለዘለቄታው ሕያው ሆኖ መኖር እንዳለበት፣ ለሰው ክብር የሚያስቡ ኢትዮጵያውያን ሁሉ የሚያምኑበት ሃቅ ነው።

ይህ ቦታ እንደማንኛውም ሕጋዊ ርስትነት አስፈላጊዎቹን የባለቤትነት ሠነዶች በተገቢው ሥርዓት አሚልቶ የሚገኝ እንደመሆኑ መጠን፣ በግል ርስትነት በሕጋዊ ካርታ ተመዝግቦ ለዓመታት የኖረ ንብረት ነው። ይህም የባለቤትነት ማስረጃዊ ሠነድ በጃችን ይገኛል።

ይህን ቦታ አባታችን የተሰጣቸው በዘመኑ በነበረው የክህነት አገልግሎት መሠረት ነው። ቦታው በተሰጣቸው ወቅት ያ ቦታ ማንም ባለቤት ያልነበረውና በተፈጥሮው በጠፍነት እንዳለ ያገኙት ነው። ቦታውን ሰው እንዲኖርበት ለማድረግ እኒያ ክቡር አባት ዕድሜያቸውን ሙሉ ባለ በሌለ ሙሉ አቅማቸው ደክመውበታል። መቸም ገዳም ይመስል ስለነበረው ስለዚያ ክቡር ግቢ በቅርቡ የተመለከተ ገለልተኛ ሰው ቢተርከው በጣም የተሻለና አስተማማኝ ድርሣን ሊሆን ይችል ነበር።

ያንን ገነት የመሰለ የመኖሪያ ግቢ፣ በጊዜው ለመልቀቅ የተገደድነው፣ ታላቁ የአፍሪቃ አዳራሽ፣ በአቅራቢያው በመሠራቱ ነው። ያ የአፍሪቃ አዳራሽ በታነፀ ጊዜ እኛ ብቻ ሳንሆን በሠፈሩ የነበሩት ዘርዓ-ካህናት በሙሉ ወደሌላ ሥፍራ እንዲዛወሩ ተደርጓል። እዚህ ላይ አንድ የተለየ ነገር ቢኖር የሠፈሩ ካህናት በሙሉ ለቦታቸው ምትክ፣ ለቤታቸውም ግምትና ማፍረሻ የተሰጣቸው ሲሆን፣ የእኛ ቤተሰብ ግን በነበሩት ታዳጊ ልጆቹ ምክንያት አቤቱታ ቀርቦ ቦታው እንዲቆይልን ለማስፈቀድ መቻ

ላችን ነው። ለዚያውም ቢሆን ከፍተኛ መራራ መከራ ታይቶበታል። ስለዚህም ነው ዛሬ ይህን ታሪካዊ በሆነ ሽፍጥና ልዩ ተንኮል አማካይነት ከቤተሰቡ ውጭ ማንም ሰው ቢሆን ሊወስደው የማይችለው።

በርግጥም እንደተባለው እርስዎ ይህን ቦታ በሆነ መልክ ንብረቴ ነው ብለው ገብተውበት ከሆነ እነዚያ የጊዜያችን ጥሬ ባንዳዎች (ው-ሻ) ከሚንቀለቀል እሳተ-ነበልባል ውስጥ ጎትተው እንደማገዱዎ፣ ከወዲሁ ሊያውቁት ይገባል። እርስዎ ቦታውን እንደግል ባለቤትነት ሊጠቀሙበት፣ የሕግም ሆነ የሞራል ብቃት የሌለዎ መሆኑን ሊያውቁት ይገባል። ስለዚህም ብዙ መዘዝ ሳይደርስብዎና ያለችዎ ጥቂት ጥሪትዎና ንብረትዎ ሳይባክን እጅና እግርዎን ከቦታው ማራቅ ብቻ ሳይሆን ለዘለቄታው፣ ዓይኖችዎንም በዚያ ቦታ ላይ ከማንሸዋረር ይቆጠቡ ዘንድ፣ በጥብቅ አሳስበወታለሁ!

ከርስዎ በፊትም ይህን ቦታ ላለፉት ግማሽ ምዕት ዓመት ጊዜ (1950 - 2000) እንደርስዎ በፎርፌና በአቋራጭ ሊወስዱ የቋመጡና የከጀሉ፣ ብዙኃን መገለጢጦች ነበሩ። ሁሉም እንዳመጣጣቸው «ሃይ!» ተብለው ወደየበዓታቸው ተመልሰዋል። በግለ-ሰቦችና በድርጅቶች፣ በመ/ቤቶችም አማካይነት «የሻሞው» ሙከራ በየጊዜው የጦፈ ነበር። ያልተሳካላቸው ታታሪዎች ሆነው ነው የቀሩት። የዘየዱት ዘዴ ተንኮል ካቀዱት ድል አላደረሳቸውም። የቀድሞው ንጉሥ ሳይቀሩ ለቅርብ ዘመዳቸው በዳረጎት መልክ ለመቸር ሞክረው ነበር። ሙከራቸው ከግብ ሳይደርስ የመሸ ጊዜያቸው ሳያስቡት ነጋባቸውና ቀረ። የደርግም ቀላጤዎች ቢሆኑ ቦታውን ወደ ግል ንብረትነት ለማዛወር ያልፈነቀሉት ቋጥኝ አልነበረም። እርሱም በበኩሉ ራሱን እንኳ ለማዳን ሳይችል በመጣበት መንገድ ተመልሶ ነጎደ። የጊዜያችን የደደቢት ደደቦች ግን «አር-ከበ» በተባለ ቀላጤያቸውና በመለስ ገፋፊነት ለርስዎ በዘር ዝምድናዎ ተላልፎ እንዲሰጥ አርገዋል። የቦታው ታሪክ ሦስተኛው ምዕራፍ እዚህኛው ዕልባት ላይ ደርሷል።

ለጊዜው የዚህ ቦታ ካርታዊ ሠነድ በጄ የማይገኝ ቢሆንም እንደአስፈላጊነቱ ወደፊት በመረጃነቱ ቅጅውን ለሕዝብ አቀርባለሁ። የቦታው ስፋት ግምት ሦስት ሺህ ካሬ ሜትር ይደርሳል። በጣም ሰፊ ቦታ ነው - ባለበት የዞን አካባቢ ከፍተኛነት አንፃር። ያ ሠፈር "First Class Zone" ነው የሚባለው። ገጻዊ መግለጫ ለመስጠት ያህል፣ ከበስተፊቱ ግምባር የታወቀው የቅዱስ እስጢፋኖስ ቤተክርስቲያን ሕንፃ ይገኛል። በስተቀኙ የሴቶች በጎ አድራጎት ሕንፃ የሰፈረበት ሲሆን፣ በስተግራው ደግሞ ብሔራዊ ሆቴል የሚባለው የድሮው አሥመራ ከተማ ከንቲባ፣ ሐረጎት ዓባይ ሕንፃ ጉብ ብሎበታል። ከበስተኋላው ታላቁን ግዮን ሆቴል የሚያዋስነው ቾረት (የቡልቡላ ወንዝ) ይገኛል። (ተከታዩን የቅርብ ጊዜ ፎቶ ይመልከቱ።)




ስለዚህ ልዩ ቦታ ጉዳዩ በበኩሌ እኔም በአንድ የእንግሊዝኛ መጽሐፌ ላይ አጠቃላይ መግለጫ አውጥቼ ነበር፤ ለጨረፍታው ያህል፦ "just about 500 meters walk from the Great African Hall".

ይህን ታንኪረኛ ቦታ በሚመለከት የላይኛውን ነጥብ አስመልክቶ አንድ የተከናወነ (ትራጀዲያዊ አልለውም) ኮሜዲያዊ ድራማ ላቅርብ። በዘመነ-ነገሥት የተተወነ ነው። ከላይ እንደገለጽኩት ይህ ቦታ በግራና በቀኝ የዘመኑ የሀብት ጽንፈኞች አካበውት ነበር። በሰተቀኙ በእጅ አዙር ለንጉሡ-ነገሥቱ የበኩር ልጅ ለሆኑት ልዕልት ተናኝ ወርቅ፣ በሴቶች የበጎ አድራጎት ድርጅት የተሰጠ ሲሆን፣ በስተግራ ደግሞ የኤርትራ ከተማ (አሥመራ) ከንቲባ ለነበሩት፣ በካፒታል ለጠነቡት ኪንቲባ ደጃዝማች ሀረጎት ዓባይ የተሰጠ ነበር። እኛን ከነዚህ ሁለቱ የዘመኑ የንዋይ ኃያላን ዲታዎች መካከል ለማስወጣት ከፍተኛ የአጣብቂኝ ትግል ይካሄድ ነበር። እንዴውም ያ አካባቢ የቤተሰቡ አምባና መናኸሪያ እንዲሆን በማሰብ፣ ቦታው ለግራዋ ክንፍ ተወላጅ ለሆነችው ጽጌ ማርያም አበበ (የልዕልት

ተናኘ ወርቅ ልጅ) ለቀኙ ክንፍ ተወላጅ ለሆነው ሥዩም ሀረጎት እንዲሰጥ ተወስኖ ነበር። ሁለቱ ግለ-ሰቦች ሚስትና ባል መሆናቸው ነው። ይህ ደባና ተንኮል በሚሸረብበት ወቅት ሁሉ የቦታው ባለ አንጡራ ሀብቶች፣ ልንጠፋ የምንችልበት ሥሌት ጠዋት ማታ ይጻፍ ነበር። በጊዜው እኔም እንዳቅምኪ የታቃውሞ አርቲክል በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ጽፌ ነበር፣ ለሣምንት ያህል ታሥሬበታለሁ። ያንን የመሰለ ጣጣና ፈንጣጣ ሲያሳልፍ የነበረ ቦታ መሆኑን የዛሬዎቹ የአደባባይ ዘራፊዎች ሊያውቁት የሚገባ ይመስለኛል። ዘርዓ - መሣፍንቱ ቦታውን ለግላቸው ለማድረግ የጣሩትን ያህል የኛ የባለቤቶቹ ንፁሐን ጦስ ጠራርጓቸው ጠፋ። ያንን የማይለወጥ ፍትሕ ከዛሬውም መንግሥት ነኝ ባይ ዘራፊ ቡድን የምንጠብቀው ነው። ልማደኛው ጦሳችን ይዟቸው ምድረ-ፋይድ ይወርዳል። በቅርብ ጊዜ - ሁለት ደመራ ሳይቃጠል!

በዚህ ሁሉ አንፃር እኛ ይህን ታሪካዊ አንጡራ ንብረታችንን የምንፈልገው፣ ሊሰጠው በሚችለው ሽርፍራፊ ብርና ጊዜያዊ ጥቅም ገጽታ ሳይሆን፣ ከቤተሰባችን ታሪክ፣ ከወላጆቻችን መታሰቢያነት፣ ከልደት ቦታችን ቅርሥነት፣ ከግል ታሪካችን ኑሮአዊ ዝንባሌ የተነሳ ነው። ሊሰጠን የሚችለውን ዕሴት ካለፈውና ከሚመጣውም ሕይወታችን ሂደት ጋር በተራዛሚ ዕይታ ስለእምናየው ነው። ለኛ በዚያ ቦታ ላይ ለታላቆቹ ወላጆቻችን ቋሚና ነባር መታሰቢያ ሐውልት አሠርተን፣ በነሱ ስም በሚጠራው ቤተ-መጻሕፍት ቤትና መሰብሰቢያ አዳራሽ፣ ለሕዝብ በምንሰጠው አገልግሎት፣ በምናገኘው ተድላ - ደስታ ባሻገር ሌላ ነገር አንመኝም። ለዚህም ዓለም መስተንግዶ በመጣንበት ወቅት፣ ስንወለድ ዕትብታችን የተቀበረበት ቦታ በመሆኑ ከፊል አካላችን በዚያ አፈር ውስጥ እንዳለ ሁልጊዜ ይሰማናል። ጥንታዊው የሀገራችን መጽሐፍም በቀደምት ብሒላዊ ጥቅሱ እንዳለው «ለብእሲ ሠናይ መቅበርቱ ዲበ ርስቱ» (ለመሬታዊ ፍጡር ሰው ከገዛ መሬቱ ላይ ከመቀበር የበለጠ ሌላ ተድላ፣ ደስታ አይኖረውም!)። ያንን ቦታችንን በሕግ ለማስከበር ይህ ጥንታዊ ጥቅስ በያዘው ቁልፍ ሀሳብ መሠረት ብቻውን በቂ ማስረጃ በሆን ነበር። አንፃራዊ ትርጓሜው ሰው በልደቱ ቦታ ምክንያት ሲጋደል ቢወድቅ ክብር እንጅ ቅሌት እንዳይደለ ያስረዳል። ያገሬ ሰው «... ያውሬ መውለጃ ይሆናል እንጅ» እያለ ሲፎክር የኖረው አፅመ-ርስቱን ባለአንጣ እየነጠቀው ስላስቸገረው ነው። ያንን ለማለት እኔስ ምኔ ይጎድለኛል?

በአሁኑ ጊዜ ከቤተ-ሰባችን የግንድ ሐረግ፣ በሕይወት፣ የምገኝ እኔ ብቻ ነኝ። በጉዳዩ ልዩ ኃላፊነትና አደራ ይሰማኛል። ያለፉትን ሦስት አሠርታት ፀሊም አዝማናት ያሣለፍኩት በተለያዩ የባዕዳን ሀገሮች ውስጥ በስደት ነው። እነዚህን ጥቁር የስደት ዘመናት በየሀገሩ ስንከራተት ያሳለፍኩት ውድ ሀገሬንና ክቡር ወገኔን ጠልቼ ሳይሆን በየጊዜው ሥልጣን ላይ የወጡ ተንባላት በተፈራረቁበት መንግሥታቸው አማካይነት ይፈጽሙብኝ የነበረው ፍዳና ዳይን፣ መከራና መቅሰፍት ስላንገሸገሸኝ ብቻ ነው። ያለኝም የተሻለ አማራጭ ስደት ብቻ በመሆኑ ነው። እንደ ሰው ማለትም እንደማንኛውም ሰብዓዊ ፍጡር የምኖርበት ትንሽ ቦታ ቢኖረኝ ወንጀልም ኃጢአትም አይደለም። ስለዚህም ከዘመናት ስደት በኋላ ወደተገኘሁበት ምድሬ ስመለስ በመኖሪያነት ልጠቀምበት የምፈልገው፣ ሌላ የሰው ቤት ሳይሆን በራሴና በግሌ አንጡራ መሬት ላይ ነው። ይህንንም ተፈጥሮአዊ መብቴን ማንኛውም ምድራዊ ኃይል ቢሆን ሊከለክለኝና ሊነፍገኝ ከቶ አይችልም። ከዋናው የቤተሰብ ሐረግ በሕይወት ተርፌ የምገኝ እኔ ብቻ ልሁን እንጅ የቤተ-ሰቡ ትውልድ ያስገኘው ዘርፈ ሐረግ ቢቆጠር ዕልፍ አዕላፍ ነው። በተጨማሪ ደግሞ የጉራ ቁልቁላ ነፋህ አለያም የቡፋ ታምቡር ደለቅህ አትበሉኝ እንጅ ከ90% በላይ የሚሆነው ወገኔ የሀገሬ ሕዝብ በዚህ ሕጋዊ የቦታ ጥያቄዬ ላይ ከጎኔ የሚሠለፍ መሆኑን የምገልጸው በሃቀኛ ትምክሕክትና በሚዛናዊ ኩራት ነው።

ነገ ሊወርድ በሚችለው የፖለቲካ ቦናና እርቃናቸውን ጥለው ለዋይዋይታ የተዘጋጁት እነስም አይጠሩ የወያኔ ተንባላት፣ በአረጠ ዕብሪታቸው፣ እንደሰካራም ቱፍታ በየቦታው እየረጩ «በገዛ ሀገርህ ላይ ቦታ የለህም» ቢሉ ማን አምኖ ሊቀበላቸው ይችላል? እነአርከበ ይህን መሰል የቤት ዘረፋ እርምጃ የወሰዱት፣ ባይገርማችሁ በጊዜው ዲሞክራሲያዊ ምርጫ ተደርጎ ከነበራቸው ሥልጣንና ኃላፊነት በብዙ ድምፅ ተተፍተው በተዘረሩበት ወቅት ነው። ስለዚህም መሬቱን በሚመለከት ያሳለለፉት ውሳኔ ተፈጻሚነት የለውም። ከፈለጉ፣ ለዘመዳቸው የናታቸውን ርስት መስጠት ይችላሉ።

የዚህን ታሪካዊ ቦታ አያያዝ ሁኔታ መግለፅ፣ አባታችን ለዚያ ቦታ ምን ያህል ከፍተኛ ክብርና ሞገስ ሰጥተው እንደነበር ሊያመላክት ይችላል። ቦታው ሲሰጣቸው ገና ጥሬ ጠፍ ነበር። በተፈጥሮው እንዳለ ያለ ነበር። የሰው እግርም ረግጦት የሚያውቅ አልነበረም። ያንን ”barren and wild” ጠፍ ቦታ እንዴት አድርገው አሸብርቀው እንዳስዋቡት ሌላ በጊዜው ቦታውን የተመለከተ ታዛቢ ቢመሰክር ይመረጣል። እንዴው ለዕይታው ያህል መለስተኛ ንድፋዊ የሆነ መግለጫ መስጠት ይቻላል።

ባጠቃላይ አራት ዓይነት የተለያዩ መደቦች ነበሩት። የመጀመሪያው ማርገጃው ነው። ከትልቁ በድንጋይ ግንብ ከተሠራው ሠቀላ ቤት ፊት ለፊት የሚገኘው፣ መለስተኛ በለምለም ሣር ያሸበረቀ ቦ

ታ ነው። ትልቁ ቤት ራሱ፣ አንድ ራሱን የቻለ ሕንፃ ቤተ-ክርስቲያን ይመስላል። መቅደስ አይኑረው እንጅ ቅድስትና ቅኔ ማኅሌት በይዘቱና በቅርፁ በተሟላ መልኩ ነበረው። እኔ ምንጊዜም ሲደንቀኝ የሚኖረው፣ መምሬ የየትኛውንም የዲዛይን ት/ቤት ያልረገጡ ከመሆናቸው ባሻገር ምንምዓይነት ከፍተኛ የኢንጅነሪግ ዩኒቨርስቲ ገብተው ያልተማሩ መሆናቸው ሲታወቅ ያንን ቦታ ከአራት ክፍላት ላይ መድበው ማራኪ የሰው መኖሪያ እንዲሆን ለማድረግ መብቃታቸው ነው። ሁለቱን ረባዳ የግራና የቀኝ ቦታዎች ለተለያዩ ዕፀዋት ማምረቻ ሲያደርጉ በስተወንዙ በኩል ያለውን ክፍል ደግሞ ማገዶ ለሚሆኑ ተክሎች ማብቀያ አድርገውት ነበር። በነዚህም ቦታዎች ላይ የሚመረተው ተክል እንደጌሾ፣ ኮባ፣ ጤና አዳም፣ ጠጅ ሣር፣ አሪቴ (ሽቶ)፣ ዳማከሴ... ብዛቱ እጅግ በሽበሽ ነበር። የሚገርመው ደግሞ፣ መምህር አልኮል የሆነ ነገር አይቀምሱም። ሰዎች መጋበዣ የሚሆን ጠላና ጠጅ ለማዘጋጀት ሲሉ ግን፣ ጌሾ በብዛት ያመርቱ ነበር።

የቤታችን ዙሪያ ግቢ የታጠረው በደረቅ የካብ ግንብ ነበር። ታዲያ የግንበኛነት ጥበብ ትምህርት ኖሮአቸው አይደለም። ያ ሁሉ ፀሐይና ዝናብ ሲወርድበት አንድ ጊዜም ተንዶ አያውቅም ነበር። የቆሻሻ መጣያው ክፍል ላስተዋለው ሰው ስለ ዘመኑ የኢንቫይሮሜንት አጠባበቅ ዕውቀቱ አስቀድሞ ያላቸው ይመስሉ ነበር። በ1950 ዓ. ም. ላይ የአፍሪቃ አንድነት ድርጅት ሕንፃ ተፈጽሞ እንዳለቀ፣ ቤታችን ያለምንም ግምትና ማፍረሻ እንዲፈርስ ሲነገራቸው የልቅሶ ያህል ክትክት ብለው መሣቃቸው ምንጊዜም የማልረሳው ትዝታዬ ነው። ባጭሩ ያን ያህል ደክመው ያለሙትን ቤትና ቦታ ልቀቁ ተብሎ ሲነገራቸው ራሳቸውን ያፅናኑት «እግዚአብሔር ወሀበ፣ ወእግዚአብሔር ነሥዓ» በሚለው ቃል ነበር። በመጭው ዘመናችን ግን ሕዝባዊያን ጉዳዮች ሁሉ ከፍተኛ ዕድገታዊ ኪደትና ዕሴታዊ ፍትሕ የሚለገሳቸው በመሆኑ፣ በበኩሌ ከብዙ ዘመናት ውጣ ውረድ በኋላ፣ እንደመምሩ «እግዚአብሔር ወሀበ... » ብዬ ያን የትውልድ ቦታ በፎርፌ የምለቅ አይደለሁም።

በኔ አቅም እንኳ ለዚያ ቦታ መተከል ሲባል ከኻያ ዓመታት የበለጠ በግብረ ዲቁና ሥራ የወጣትነት ለምለም ዘመኔ እስኪጠወልግ ድረስ አገልግያለሁ። ብዙ የተለያዩ ከባድ ፈተናዎችንም አይቼበታለሁ። ታዲያ እንዴትና ለምንስ ነው ገና ለገና ከምድረ-ትግራይ በመወለዱ ብቻ ይህ ቦታ ሽልማት ተደርጎ ይሰጠዋል? በጭራሽ! ሊደረግ አይችልም!

አሁን ይህ ቦታ በዳረጎትነት ተሰጠኝ ብሎ የሚጨፈረውና ጮቤ የሚረግጠው ሰው በቀጣዩ የፍትሕ ወቅት የደም ዕንባ ከሚያለቅስ ዛሬውኑ አስረክቦ ዞር ቢል ይመረጣል። በዚህም ፍትሓዊ ድርጊቱ ከበስተኋለኛው ፀፀት ሊድን ይችላልና የሰብዓዊነት መልዕክቴንም እልካለሁ።

<u>መከርቸሚያ</u>

«.... ባያውቁት ነው እንጅ - የእኔን ቋሚ ንግርት፣
በተወለድኩበት ነው - የምቀበርበት፣
ሌላ ቦታ ሳይሆን - በትውልዴ መሬት።

አስቀድሞም ቢሆን - ዕትብቴ ተቀብሯል፣
ቀሪውም አካሌ - በርግጥ በክብር ያርፋል።

ሲንከራተት ኖሮ - አካሌ የትም ምድር፣
በስተመጨረሻ - የሚያርፍበት አፈር፣
ከተወለድኩበት ነው - በክብር የሚቀበር።

በመቃብሬም ላይ - በስተራስጌው በኩል፣
«እኔም እንደርስዎ - ሕያው ነበርኩ!» የሚል፣
በትልቅ ቋጥኝ ላይ - ተቀርፆ ይፃፋል።

ይኸ ሁሉ ንግርት - ከወዲሁ ታውቋል፣
ከዚያ ርስት ለመንቀል - ታዲያ እንዴት ይቻላል!!

(ገሞራው 1999)

(ጦማር 2 ይቀጥላል)